የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር - ዴሞክራሲያዊ ምትሕብባር ትግራይ

TIGRIAN ALLIANCE FOR NATIONAL DEMOCRACY (TAND)

e-mail: ezanareg@hotmail.com

# ሽንፈት የማይቀበል ፤ ውርደት ይጨምራል!!

የአምባገነኖች ባህሪ ምንጊዜም ቢሆን በራሳቸው ጭፍን አመለካከት ተጠፍረው መሄድ ካልሆነ በስተቀር የህዝቡን ድምፅ ከቶውንም አያዳምጡም ። ለዚህም ነው መጨረሻቸውን ውርደት ለብሰው የሚቀበሩት ። ከዚህ በፊት በዓለም ላይ የታዩ አምባገነን መሪዎች ሁሉ የሄዱበትን አቅጣጫ መለስ ዜናዊም ተያይዞት ይገኛል ።

በተለይ የመለስ አወዳደቅ ልዩ የሚሆነው ግን በህዝቦች መካከል አደገኛ የጥላቻ ፖለቲካ ዘርቶ ለመውረድ በመዘጋጀቱ ነው ።

የግንቦት 7ቱ ምርጫ መለስ በፈጠረው ምርጫ ቦርድ ፤ ከቀበሌ በታች ወርዶ እስከ ጎጥና ቤተሰብ ድረስ በተዘረጋ መዋቅር እንዲሁም በአፋኝ ካድሬዎቹ የተተበተበ ቢሆንም ህዝቡና ታዛቢዎች ለመቆጣጠር በቻሉበት አካባቢ የኢህአዴግ መሪዎች እርቃናቸው ወጥተው ሽንፈትን ተከናንበዋል ። እንዲያው ነው እንጂ ከምርጫው ቀን በፊትም ከሁለት(2) እስከ ሶስት(3) ሚልዮን የሚገመት የአዲስ አበባ ህዝብ አደባባይ ወጥቶ በቃቹህ ውረዱ ብሏቸው ነበር ። አምባገነኖች ህዝብን አያዳምጡምና ውርደት እስኪጨምሩ ድረስ ሥልጣን ላይ ተንጠልጥለው እያጭበረበሩ መቆየታቸው አልቀረም ።

እዚህ ላይ በምርጫው ሶሞን የተከሰተውን ትልቅና ሀፍረተቢስ የኢህአዴግ ማጭበርበርን መመልከቱ አስፈላጊ ይሆናል ። መለስ ዜናዊ ከአንድ ሚልዮን በላይ የአዲስ አበባ ህዝብ ኢህአዴግን ደግፎ ወጣ በተባለው ህዝብ ፊት "እኛ ይህ ሁሉ የህዝብ የድጋፍ ማዕበል ይዘን በምርጫው ማጭበርበር ለምን ያስፈልገናል" እያለ በተቃዋሚ ላይ ሲያቅራራ ተደምጧል ። ጥያቄው እንግዲህ በአዲስ አበባው ምርጫ ኢህአዴግ በዜሮ (0) ሲረታ ያ የህዝብ ማዕበል የተባለለት ደጋፊ የትገባ ? የምርጫ ካርዱንስ ወዴት ጣለው ? ብለን ለመጠየቅ እንገደዳለን ።

መልሱ ግልፅ ነው ። ያ በማዕበል የተመሰለው የኢህአዴግ "ደጋፊ" ህዝብ ለተቃዋሚው ወገን ድምፁን ሰጥቷል ወይም ኢህአዴግን ከመምረጥ የምርጫ ካርዱን ቀዳድዶ ጥሎት ቢሆን እንጂ ኢህአዴግ በዜሮ (0) ባልተሸነፈ ነበር ። ስለዚህም ያ የህዝብ "ማዕበል" የኢህአዴግ ደጋፊ ነው እየተባለ የተቅራራብን ተገዶ የወጣ የውሸት ደጋፊ እንደነበር በማያሻማ መንገድ የአዲስ አበባ የምርጫ ውጤት ሀቁን አሳይቶናል ። እንግዲህ ዓለም አቀፍ ታዛቢ ፤ የተደራጀ ተቃዋሚ ፤ ሲቭክ ማህበራትና አንጻራዊ ነፃ የመገናኛ ብዙኃን ባለበት ዋና ከተማ ያንን ያህል ደፍሮ የሚያጭበረብር ኢህአዴግ ይህ ሁሉ ታዛቢ በሌለባቸው በትናንሽ ከተሞችና በገጠራቱ ኢትዮጵያ ምን ዓይነት ሸፍጥ እንደሚያካሂድ ለመረዳት ብዙ ትንተና አያስፈልገውም ።

ትግራይን እንመልከት ፤

የኢህአዴግ ማሌሊታዊ/ስታሊናዊ የአፈና መዋቅር ሥር የሰደደው በትግራይ ምድር ነው ። በትግራይ ውስጥ ያለው ህዝብ ነፃ ጋዜጣ እንዳያነብ ፤ የሌላ ተቃዋሚ ድርጅት ድምፅ እንዳይሰማ ፤ እንዳይደራጅ ፤ እንዳይደግፍ በጨካኝ ካድሬዎች ተጠፍሮ ተይዟል ። ይህ ክስተት በደርግ ቀይ ሽብር ወቅት "የፀረ አብዮት ፅሑፍ ያነበበ ፤ ያስነበበ ፤ ሲያነብ ያየ . . . " ከሚለው አዋጅና እርምጃ ብዙ የተራራቀ አይደለም ። አፈናው በህዝቡ ላይ ቀርቶ

ለመንቀሳቀስ ሙከራ ባደረጉ የተቃዋሚ ድርጅቶች ላይም እንደወረደ አይተናል ። አፈናውና ወከባው አላንቀሳቅስ ስላላቸው ከውድድሩ መውጣትም ግድ ሆኖባቸዋል ። ኢዴፓን ከመቀሌ እንዲወጣ የተገደደበት ሁኔታም ይህንን በግልጽ ያሳያል ።

ተወዳዳሪም ሆነ ታዛቢ በሌለበት ፤ ካድሬና "የፀጥታ" ነጭለባሽ እንደልቡ በሚረግጥበት ትግራይ ምን ዓይነት ምርጫ ሊካሄድ እንደሚችልና ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል ገና ከጅምሩ ግልጽ ነበር ። ብቻውን የተወዳደረ ብቻውን አሸናፊ መሆኑ አይቀርም ። ይህ በትግራይ ህዝብ ላይ የተጫነው አስከፊ አፈና በደርግ የአገዛዝ ዘመን የነበረው የካድሬና የቀበሌ አፈናን እንድናስታውስ ያደርገናል ። በደርግ አገዛዝ ያለፈ ታጋይ ሁሉ አፈና ምን እንደሆነ ጠንቅቆ እንደሚረዳ አንጠራጠርም ። በትግራይ ህዝብ ላይ የህወሓት/ኢህአዴግ መሪዎች የጣሉት አፈናም ከደርግ አፈና እንደማይለይ ታጋዩ የኢትዮጵያ ህዝብ ይስተዋል ብለን አናስብም ። ከምርጫው ሶስት ቀናት በፊት መለስ ዜናዊ መቀሌ ከተማ ውስጥ ለሚወዳደረው ታማኝ ካድሬው አዲስዓለም ባለማና የትግራይ አስተዳዳሪ ለሆነው ፀጋይ በርሀን "መቀሌን የግድ ማሸነፍ አለባቹህ" ብሎ አምባገነናዊ ትእዛዙን ሲሰጥ እሺ ብለው የተቀበሉት አሽከሮቹ በመቀሌ ህዝብ ላይ ያወረዱት አሳፋሪ ዘመቻና ወከባ በተቃዋሚዎች ላይ ያደረሱት ሽብር በዝርዝር ከነጭብጡ በሌላ ፅሑፍ የምንመለስበት ርእሰ ጉዳይ ይሆናል ። ከርቀት ምርጫውን የታዘቡት አንዷት የኤውሮጳ ህብረት ቡድን አባል ወይዘሮ "ታዛቢዎች በነበርንበት አከባቢ ሁሉ ተቃዋሚዎች አሸነፉ ፤ ታዛቢዎች ባልነበርናቸው አከባቢዎች ደግሞ በሙሉ ኢህአዴግ አሸነፈ ፤ ይህ ምርጫው ከባድ ችግር እንደገጠመው ያሳያል" ያሉት በጥቅሉ ትግራይና ሌሎች ከአዲስ አበባ ራቅ ያሉ አከባቢዎች ያሉበትን የአፈና ሁኔታ ገላጭ ነው ።

አፍነው በመያዝ ሌላ አማራጭ ድርጅትን እንዳይመርጥ ፤ እንዳያይ ፤ እንዳያዳምጥም ያደረጉት የትግራይ ህዝብ ከልቡ እንደራቃቸው የተገነዘቡት እነመለስ/ስብሓትም አደገኛ ወደሆነው የጥላቻ ፖለቲካ ቅስቀሳ ገብቷል ። "እነዚህ ተቃዋሚዎች ሥልጣን ከያዙ የትግራይ ህዝብ አለቀልህ ፤ ያጠፉሀል ፤ ንብረትህን ይዘርፉሀል ፤ ያባርሩሀል . . . . " እያሉ ከኢህአዴግ በስተቀር መብታቸውን የሚጠብቅ ኃይል እንደሌለ ስሜት በሚነካ ፤ ፍራቻን በሚቀሰቅስ ፕሮፓጋንዳ እያስታጠቁት ነው ። አብረዋቸው የበሉ የጥቅም ተጋሪዎቻቸውም መፈክሩን ቀልበው በማስተጋባት የትግራይ ህዝብ አፈና ሲወሳ በተቃራኒው ሙግት ሲገጥሙ የነበሩ ወገኖች ፤ ዛሬ የግል ጥቅማቸው አደጋ ላይ እንዳይወድቅ በመስጋት ለትግራይ ህዝብ ተቆርቋሪ በመምሰል የጌቶቻቸውንና የራሳቸውን ጥቅም አስከባሪ ደጀን ለማድረግ ሲፍጨረጨሩ ይታያል ። በዚህ ቅስቀሳ የሚታለል ጥቂት የዋህ እንደማይጠፋ ሁሉ በአንጻሩ ደግሞ ፀረ ትግራይ ህዝብ የሚቀሰቅስ ጥቂት ፅንፈኛም አይጠፉም ። ሁለቱም ፅንፈኞች እስካሉ ድረስ ደግሞ እርኩሶቹ እነስብሓትና መለስ ክብሪቱን ጭረው ህዝብ ለህዝብ ሲተላለቅ ገላጋዮች ሆነው በመቅረብ አምባገነናዊ አገዛዛቸውን ለመቀጠል ተሰልፈዋል ። ለአንድ ወር የሚዘልቅ ፤ ሰላማዊ ሰልፍን የሚያግድ ያስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በለውጥ ፈላጊው ህዝብ ላይ የጣሉበት ሁኔታ የዚሁ አደገኛ ሴራ የመጀመሪያው ምልክት ነው ። መሰሪ እቅዳቸው እንዲሰምር ከዚህም ከዛም አንድ ሁለት ሰው ከማስገደልና የጥላቻ ፖለቲካውን ከማራገብ የማይመለሱ ክፉ ሰዎች መሆናቸው ዴሞክራሲያዊና ሀገር ወዳድ ኃይሎች ተገንዝበው ሴራው እንዲከሽፍ የህዝቡ መተሳሰር እንዳይላላና ሀገሪቱ ማጥ ውስጥ እንዳትገባ አፍራሹና ፀረ ህዝብ ቅስቀሳን አምርሮ በመቃወም ተግቶ በድፍረት መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል ። ህዝቡ ዋና ጠላቶቹ አምባገነኖቹ የኢህአዴግ መሪዎች ብቻ መሆናቸውን ተገንዝቦ በህብረት እንዲታገላቸውና በነሱም መቃብር ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ እንድትገነባ ከሁሉም በኩል ያሉትን ፅንፈኞች ለእልቂት በር ከፋች እንዳይሆኑ ነቅቶ መቆጣጠር ያስፈልጋል ። እንደብትር እንጠቀምበታለን የሚሉት ሠራዊትም የጭቁኑ ህዝብ ወገን ነውና ጣቶቹን በአምባገነኖቹ ላይ እንዲቀስር ማስቻል የሁላችን ሓላፊነት ነው ።

ኢህአዴግ ዓለም አቀፍ መስፈርትን ባሟላ እውነተኛ ምርጫ ተወዳድሮ የህዝብን ድምፅ ለማሸነፍ የሚችልበት ራእይ እንደሌለው ከዚህ በፊት ደጋግመን ስንገልጽ ቆይተናል ። አሳዳሪዎቹን አስመስሎ በማስደሰት የድጎማ በሮች ይበልጥ እንዲከፈቱለት የተወሰኑ ወንበሮችም በኮታ ለተቃዋሚ ሊለቅ እንደሚችል ደጋግመን አስታውሰናል ። ይኸው አልቀረም ፤ በምርጫው ማግስት ድምጽ ሳይቆጠር አሸናፊነቱን በይፋ አውጇል ። የህዝብን ድምጽ ቀምቶ ሥልጣን ላይ ለመቆየት የወጠነው ውጥኑን ለማሳካት አሁን ተቃዋሚን ለመከፋፈል መስራቱም አይቀርም ። ሰለሆነም ተቃዋሚው ወገን ሁኔታውን ነቅቶ በመከታተል እንዲያከሽፍና ህዝባዊ ትግሉን ወደ ታለመለት ግብ እንዲያደርስ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል ። የህዝብን ድምፅ ከኮሮጆ በጉልበት ዘርፈው ሥልጣን ላይ ለመቆየት የተደረገው የአምባገነኖች ሴራ መጋለጥ አለበት ፤ መቀልበስም አለበት ። ይህንን ለማሳካት የሚያስችል ህዝባዊ ሰላማዊ ትግል በየቦታው መለኮስና መቀጣጠል አለበት ። ትግራይ ውስጥና በብዙ የገጠሪቱ ኢትዮጵያ ምርጫ ጣቢያዎች ተካሄደ የሚባለው ምርጫ ፤ የተቃዋሚ ወገን ነፃ እንቅስቃሴ የታገደበትና የተገደበበት እንደነበረ አያጠያይቅም ። መራጩ ህዝብ ሙሉ በሙሉ በኢህአዴግ ነብሰበላ ካድሬዎች ቁጥጥር ሥር እንዲገባ መደረጉም ይታወቃል ። በዚህም ምክንያትም ነፃ ምርጫ ሊታሰብ የሚቻል አይሆንም ። ስለሆነም በትግራይና ሌሎች በተመሳሳይ የካድሬ ቁጥጥርና ወከባ ሥር ፤ ምርጫ ባካሄዱ አከባቢዎች ምርጫ እንዲደገም ፤ ቆጠራ በተጭበረበረባቸው አከባቢዎች ደግሞ ዳግመ ቆጠራ እንዲካሄድ አምባገነኖቹን ለማስገደድ እንዲቻል ጠቅላላው ህዝብና ሁሉም ዴሞክራሲያዊ የፖለትካ ኃይሎች ከፍተኛ ትግል እንደሚጠብቃቸው መገንዘብ ይኖርባቸዋል ።

በኢህአዴግ ቁጥጥር ሥር ያለኸው ሠራዊት ሆይ ፦

አምባገነኖቹ የኢህአዴግ መሪዎች የሚበቃቸውን ሀብት የትም አካብተው ፤ ከቻሉ ባሉበት ለመቀጠል ካልቻሉ ደግሞ ሸሽተው የሚኖሩበት ሁኔታን አመቻችተዋል ። አሁን ህዝቡ ተነሳስቶ የማይፈልጋቸው መሆኑን በግልፅ ስለነገራቸው የመጨረሻው ቀቢፀ ተስፋ ሴራ እየተበተቡ ነው ። የጥላቻ ፖለቲካና የፍርሀት ዘመቻ በረቀቀ ዘዴ እያስተጋቡት ነው ። ሰሞኑን በማስታወቅያ ሚኒስትሩ በረከት ስምዖን "ተቃዋሚዎች የዘር ካርድ ተጠቅማቹህ አሸነፋቹህ ግን ሕጋዊ እርምጃ በመውሰድ እንለውጠዋለን " ሲል በአንድ በኩል የዘር ቅስቀሳ ሲያራምድ በሌላ በኩል ደግሞ እሱ ሕግ የሚለው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅን ተጠቅሞ በሰላም የሚቃወመውን ሁሉ ለመጨፍጨፍ እንደሆነ ሊገባን ይገባል ። ተቃዋሚው ወገን እንደሆነ የኢህአዴግ ፀረ ዴሞክራሲ አገዛዝ እንዲያበቃ አመራሩን ተቃወመ እንጂ ህዝብን የመቃወም አጀንዳም ይሁን ቅስቀሳ የለበትም ። በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ፤ በሕግ የበላይነት የምትተዳደር ኢትዮጵያ ነው አጀንዳው ። በዚህ የተቀደሰ ዓላማ ሥር የተደራጁ ኃይሎች ብዙ ናቸው ፤ ወገንህም ናቸው ። በመሆኑም ለዚህ ገንቢ ዓላማ መታገል ያንተም ሓላፊነት ስለሆነ የአምባገነኖቹ መሪዎች ቅስቀሳ ተቃውመህ የህዝብ ድምፅ እንዲከበር ከህዝቡ ጎን ተሰልፈህ ጥሩ ታሪክ እንድትሠራ ይጠበቅብሀል ። ድምፅ ለማሰማት የቻለውና በአፈናው መክበድ ድምፁን ለማሰማት ያልቻለው ወገንህ ለመብቱ መከበር ፤ ለሰላምና ለኑሮው መሻሻል በሚያደርገው ትግል ከጎኑ እንድትሰለፍ ይጠብቃሀል ። የወደፊት ዕድልህ ከአገርህና ከህዝብህ ጋር እንጂ ነገ ጥለዉህ ከሚፈረጥጡት ስግብግብ አምባገነን መሪዎች ጋር እንዳልሆነ አውቀህ አሁኑኑ ከህዝብህ ጋር ወግነህ የህዝቡን ድምፅ ተግባር ላይ እንዲውልና የአምባገነኖቹ ሴራ እንዲከሽፍ አድርግ ። “የነመለስን ሴራ ከህዝባችን ጎን ተሰልፈን እናከሽፍ” የሚለው ጥሪ አስተጋባ ።

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ህዝብ ወደ ህዋላ የማይመለስ የሥልጣን ምንጭና ባለቤት መሆኑ የሚያረጋግጥበት አንድ አዲስ ምዕራፍ ላይ ደርሷል ። ገዥዎችን ሳይፈራ በመብቱ ተጠቃሚ መሆን ጀምሯል ። አምባገነኖቹ የህዝቡን መብትና ወሳኝነት ሥር እንዳይሰድ በእንጭጩ ለመቅጨት አደገኛ የጥላቻ ፖለቲካና መርዛም የፍርሀት ዘመቻ እየነዙበት ነው ። በርግጥ የቀራቸው ምርጫ ፤ ሥልጣን ለህዝብ ማስረከብ ወይም ወደ ሙሉ ፋሽሽትነት

መሸጋገር ቢሆንም አምባገነኖቹ ሁለተኛውን የፋሽሽትነትን መንገድ የመረጡ ይመስላል ። ለዚህ እኩይ ሴራቸው ተባባሪ የሚሆኑ የዋሆችና አድርባዮች ስለማይጠፉ ህዝቡ ከነዚሁ አደገኛ የጥፋት መልእክተኞች ሴራ ራሱን እየጠበቀ ትኩረቱ በዋናው ጠላት ላይ እንዲሆን በአፅንዖት ስናሳስብ ፤ የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር (ት.ዴ.ት) ከኢትዮጵያ ህዝብ ጎን በመቆም ለሰላም ለአንድነት ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና ለሕግ የበላይነት መንገሥ የሚያደርገውን ትግል በሰፊው ይቀጥልበታል ። በተረፈ ዘርፈ ብዙዉን የኢትዮጵያ ችግር ለመቅረፍ የአገር ወዳድ ዴሞክራቶች ከህብረት የላቀ ውህደትም እንዲፈጥሩ ደጋግሞ ይጠይቃል ። ይህ አቅጣጫ ነው የአምባገነኖቹን ውድቀት አቀላጥፎ ዘላቂ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መሥርቶ የኢትዮጵያን ትንሣኤ የሚያረጋግጠው ። በመጨረሻም ኢህአዴጎች ውርደት ሳይጨምሩ ሽንፈት ቢቀበሉ ለሁሉም ይበጃል እንላለን ።

ድል የህዝብ ነው ! ! !
የአምባገነኖች ሴራ በህዝብ ህብረት ይከሽፋል ! ! !

ት.ዴ.ት
ግንቦት 1997 ዓ.ም